# በእድሜ ተለቅ ያሉትን ሰዎች ያላግባብ ማጐሳቆል



ጽሁፋዊ መግለጫ

## ገንዘብንና ንብረትን ደህንነቱ በተጠበቅ ስለማስቀመጥ

ይህ መረጃ በካክቶን ህጋዊ ማእከል (Caxton Legal Centre) ካለው **የእድሜ አንጋፋ ህጋዊና የድጋፍ አገልግሎት** (Seniors Legal and Support Service) የቀረበ ነው። አገልግሎቶች የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙት በአስተዳደር ግዛት መንግሥት በኩል ነው። ታማኝ በሆኑ የቤተሰብ አባላት ወይም በጓደኞች በኩል ለአንጋፋ የሆኑ ሰዎች ጉዳት ወይም የማግለል ችግር ጋር በተዛመደ ያለክፍያ በነጻ፣ ሚስጥራዊ የሆነ የህጋዊና ማሕበራዊ ሥራተኛ አገልግሎቶች ይቀርባል።

### እንዴት በነጻ ድጋፍ ማግኘት እንደሚቻል — ደረጃ በደረጃ

ማጐሳቆል በገንዘብ ፋይናሻል፣ በመስደብ፣ በስሜት፣ ነአካል ወይም እነዚህን በማጣመር ሊሆን ይችላል። ብዙጊዜ ስለነዚህ መነጋገር ከባድ እንደሚሆን እና ስለተፈጠረው ድርጊት መነጋገሩ አሳፋሪ እንደሆነ የተለመደ ነው። ካሳሰብዎት ወይም ፍርሃት ከተሰማዎት ታዲያ የርስዎን ሁኔታ ለማሻሻል ስላለዎት ምርጫዎች ለማወቅ ከፈለጉ፣ በሞላው አስተዳደር ግዛት የእርዳታ መስመር በስልክ 1300 651 192 አድርጎ መደወልና እርዳታ መጠየቅ።

## የተለመዱ ታሪኮች

### የአንጋፋ ሰዎች ገንዘብ እና ንብረቶች አላግባብ መጠቀም ሊሆን ይችላል

በየቀኑ ብዙ አንጋፋ አውስትራሊያኖች ገንዘባቸውና ንብረታቸው አደጋ ላይ እንዲወድቅ ይወስናሉ። የሚያበሳጨው፣ ሁልጊዜ እነዚህን መጥፎ ውሳኔዎች እንዲያካሂዱ የሚገፋፉት የቤተሰብ አባላት ናቸው። ያለዎትን ፋይናንስ በችግር ላይ እንዲገባ ማድረግ ከሚችሉት የተለመዱ ሁኔታዎች:

- ለርስዎ ቤተሰብዎ ወይም ጓደኞች ስለማበደር
- የባንክ ሰነዶችን መፈረም ይህም ለሌላ ሰው እዳ እርስዎ ሃላፊነት ስለመውሰድ (ለምሳሌ፡ በርስዎ መኖሪያ ቤት ላይ ዋስትና ወይም የማስያዣ ገንዘብ መውሰድ)
- እርስዎ የፋይናንስ ሳያገኙ ለሌላ ሰው ተብሎ ብድር ከባንክ ገንዘብ ስለመበደር
- ለርስዎ ቤተሰብ ወይም የንግድ ሥራ ገንዘብ ስለማበደር
- በርስዎ የእድሜ ጡሮታ ወይም የአንጋፋ እንክብካቤ አገልግሎቶች ስለማግኘት መቻል ላይ እንዴት ችግር እንደሚፈጥር ሳይረዳዎት ገንዘብን ማጥፋት
- ምን ያህል ገንዘብ ማውጣት እንደሚቻል ሳያውቁ በጋርዮሽ ባንክ አካውንት ላይ ያለምንም ገደብ ገንዘብ ስለማስቀመጥ
- ለርስዎ ባንክ አካውንት ወይም የሴንተርሊንክ ክፍያዎችን እንዲቆጣጠር ለሆነ ሰው ስልጣን ስለመስጠት
- የርስዎን ቤት በመሸጥ አሮጌ ፍላት/ flat ወይም በደባል መጠለያ ቤት መግዛት፣ በተለይ እድሜዎት እጨመረ ሲሄድ በቤተሰብዎ የአካል እንክብካቤ እንዲያገኙ ቃል የገቡት ካለ
- ስለርስዎ ፋይናንስ ህጋዊ ለሆነ ሰነድ (የህግ ማስገደጃ) ከመፈረምዎት በፊት ህጋዊ የሆነ ምክር ስላለማግኘት
- እርስዎን እንዲንከባከብ ነገር ግን በቂ እንክብካቤ ሳያገኙ ለአንድ ሰው የሴንተርሊን ክፍያ እንዲያገኝ ስለመስማማት
- በመስመር፣ ስልክ ወይም ከበር ወደበ እየሄድ በማንኳኳት ማጭበርበር ይሆናል።

caxton
legal centre inc

# ለምንድ ነው ነገሮች ወደ ስህተት የሚሄዱት

በእድሜ አንጋፋ የሆኑ ሰዎች በሚስማማቸው መልኩ የፋይናስ ውሳኔዎችን፤ ይህም እንዴት ከገንዘብና ንብረት ጋር በተዛመደ መደራደርና ከፊለጉም የቤተሰብ ጥቅምን ለማስጠበቅ እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻልን ያካትታል። ይሁን እንጂ ችግሮች ሊፈጠር የሚችል:

- የርስዎ አካል መዳከም፤ ጤነኛ አለመሆን፤ ለእንክብክቤ ጥገኝነት፤ ብቸኝነትና መገለል፤ የፋይናንስ መቆጥጠር ልምድ ማነስ፤ የመደናገር መጨመር፤ በቅርቡ አጋር ባለቤትን ማጣጥ በቀላሉ በአደጋ ተጋላጭ እንዲሆኑ ካደረገ
- የቤተሰብ አባል ግላዊ የሆነ ችግር ካለበት ማለት እንደ የአእምሮ ጤና ችግሮች፤ ያለው ዝምድና/ግንኙነት ከተበላሸ፤ አለመሥራት፤ ወልፈኝነት ካለበት
- በርስዎ ገንዘብና ንብረት ላይ ልክ ሁሉም ቤተሰብ አባላት ባለቤት እንደሆነ ለመቆጣጠር ቤተሰብ ልማድ ካለበት
- ቁልፍ በሆኑ የፋይናንስ ውሳኔዎችን ከማካሄድዎ በፊት የራስዎ የህግ አማካሪ ወይም የፋይናንስ አማካሪ እንዳላገኙ ነው።
- በፊርማ የተረጋገጠ ጽሁፋዊ ስምምነት ከሌለ፤ በንግግር ቃል መግባት
- የጥንካሬ መፈስ ከሌለዎት ወይም በርስዎ ላይ ያለን ውጥረት 'አይሆንም' ለማለት በርስዎ ላይ በቂ ስጋት ካለ
- እርስዎ ስለሚያሳስብዎት እንዳይናገሩ የቤተሰብ ባህልና የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ያስቆምወታል
- ስለላቸው ውርስ ወይም ስግብግብነት የቤተሰብ አባላት የሚጠብቁ ከሆነ
- የርስዎን ችግሮች የሚናገርና የሆነ ነገር ማለት የሚችል ማንም ሰው ከሌል
- ከፋይናንስ ጋር በተዛመደ ሊረዳዎ ያመኑት ሰው ስለ ውሳኔዎች የማያማክርዎ ወይም በጽሁፍ ወረቀት የማያሳይዎት ከሆነ
- እርስዎን ለመከላከል ባንኮች እርምጃዎችን የማይወስዱ ከሆነ
- ባለብዎት የቋንቋ ችግር ለመወጣት አስተርጓሚ ካልተጠቀሙ
- በአቃቤ ህግ በኩል በስህተት ጥቅም ላይ እንዳይውል ለማስወገድ የህግ ማስገደጃ ሰነድ በሚገባ እንዳልወጣ ነው።

# ገንዘብና ንብረት አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል እንዴት ስለሚቀመጥ

የርስዎን ገንዘብና ንብረት ደህንነቱ በተጠበቀ ለማስቀመጥ በጣም ጥሩ የሆኑ ዘዴዎች:

- ከሚያምኗቸው ከጓደኞች፤ ቤተሰብ፤ ከፋይናንስ ኤክስፐርቶች፤ ከእድሜ ትልቅ ቡድኖች፤ ከፋይናንስ እርዳታ መስመር ጋር በመነጋገር ስለላለዎት ፋይናንስ በበለጠ መረዳት
- ለፋይናሻል ማረጋጊያ ሠራተኛ (እንዴት ገንዘብን መቆጣጠር እንደሚቻል በተሻለ ስለመረዳት) ወይም ለፋይናሻል አማካሪ ማነጋገር (ከእዳ ጋር በተፈጠረ የፋይናሻል ችግሮች ስለመደራደር)
- ወደ ቅንጅት ውስጥ ከመግባትዎ በፊት ለርስዎ የሚሆን ህጋዊ አማካሪ እና ፋይናሻል አማካሪ ማግኘት (ቤተሰብ አባላ ወይም ጓደኛ ወደሚሄድበት ተመሳሳይ አማካሪ አለመሄድ)
- የርስዎ ህጋዊ ማስገደጃ ሰነድ ሙሉ በሙሉ መከላከያ ስለሚያቀርብልዎት ማረጋገጥ። ህዝባዊ ባላደራ ወይም የግል ህግ ጠበቃ ይህንን ሰነድ እንደገና እንዲታይ ሊረዳዎ እንዲችል
- በብዛት ጽሁፍ ደብዳቤዎች ወይም በሚያስፈልግበት ላይ አስተርጓሚ እንዲጠቀሙ በመገፋፋት ስለዚህ ሁሉንም ቅንጅቶች እና መፈረም ያለባቸውን ሰነዶች ይረዳዎታል
- በርስዎ ጡሮታ ወይም እድሜ እንክብካቤ አገልግሎቶች ላይ እንዴት ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ለመረዳት ከሴንተርሊንግ ጋር መነጋገር (ከፋይናንስ መረጃ ሀላፊዎች)
- የቤተሰብ ቅንጅትን በጽሁፍ ለማስቀመጥ እና እያንዳንዱ በነዚህ ላይ ይፈርማሉ
- የርስዎን ገንዘብ ደህንነት ባለው ስለማስቀመጥ ወደ ባንክ በመሄድል ፤ በተለይ ከኢንተርኔት ባንክ ልውውጥ፤ ሚስጥራዊ ቁጥሮች/PIN numbers፤ በጋርዮሽ አካውንት እና በሶስተኛ አካል ሥልጣን ላይ ለመነጋገር ነው።

በፋይናንስ መጨናነቅ ወይም በቤተሰብ ግፊት ሳቢያ ማታ ከእንቅልፍ የሚያነቃዎት ከሆነ ስለዚህ ጉዳይ ለህኪምዎ መናገር እና ወደ ባለሙያ አማካሪ ስለመላክ መጠየቅ — ጭንቀት ካለ ጤናማ ሆኖ ለመቆየት ሊያካብደው ይችላል።

የፋይናሻል ውድቀት/ማጣት ሊያጋጥምዎ የሚችልበት ምክንያት አንድ ያመኑት ሰው ስህተት ነገር ከፈጸመ ነው። የርስዎን ገንዘብ ለመከላከል ወይም ለማስመለስ በጠቃሚ መገናኛ/Useful Contacts ስር በተዘረዘሩት አገልግሎቶች በኩል እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

# ያለ ክፍያ በነጻ እርዳታ የት ይገኛል

ለእድሜ አንጋፋ ህጋዊና ድጋፍ አገልግሎቶች

በካክቶን ህጋዊ ማእከል/ Caxton Legal Centre ላይ ለህጋዊ የሆነ ምክርና ለማሕበራዊ ሥራ ድጋፍና ውክልና

ስልክ: (07) 3214 6333

በእድሜ አንጋፋ ለሆኑ ማጎሳቆል መከላከያ ክፍል

ስልክ: 1300 651 192

ADA አውስትራሊያ/ADA AUSTRALIA

ስለርስዎ ውሳኔ አሰጣጥ መብትዎ ወይም ከእድሜ አንጋፋ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ስላለዎት አሳሳቢ ጉዳይ አውጥቶ ለመነጋገር እርዳታ

ስልክ: 1800 818 338 ወይም 3637 6000

የተውሃደ እንክብካቤ/ DIVERSICARE

ከተለያየ ባህልና ቋንቋ ያለበት ለመጡ ሰዎች ጥራት ያለው የቤት ውስጥ እንክብካቤ አገልግሎቶች ለመነጋገር እርዳታ

ስልክ: 1300 348 377

የፋይናሻል አማካሪዎች/FINANCIAL COUNSELLORS

ከመደበኛ የሆነ እዳ ችግሮች ጋር በተዛመደ እርዳታ

ስልክ: 1800 007 007

ከፖሊስ ጋር ለመገናኘት/POLICE LINK

ስልክ: 13 14 44 ወይም ለድንገተኛ ችግሮች 000

የኵውንስላንድ ህዝባዊ ባላደራ/PUBLIC TRUSTEE OF QUEENSLAND

ያለክፍያ የኑዛዜ ቃል መግለጫ እና EPAs (በክፍያ) የረቀቀ ንድፍ

ስልክ: 1300 360 044

በስልክ የአስተርጓሚ አገልግሎት/TIS

ስልክ: 13 14 50

የህዝባዊ መጉዚት ተከላካይ ቢሮ/OFFICE OF THE PUBLIC GUARDIAN

ለአቅመ አዳም በደረሰ ሰው የአካል ጉዳት ውሳኔ ማካሄድ አቅም አንጻራዊ ለተፈጠረ መጎሳቆል ክርክር

ስልክ: 1300 653 187

በኲውንስላንድ ውክልና የተካተተ/QUEENSLAND ADVOCACY INCORPORATED

ለህጋዊ የሆነ ውክልና የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች

ስልክ: 1300 130 582

የኲውንስላንድ ህግ ማሕበረሰብ/QUEENSLAND LAW SOCIETY

ለግል ህግ ጠበቃዎች ዝርዝር መረጃ ለማግኘት

ስልክ: 1300 367 757

የበላይ ጥያቄ መስመር/SENIORS ENQUIRY LINE

ጥያቄ ወይም ችግር ሲኖርዎ የት እንደሚኬድ እርግጠኛ ካልሆኑ

ስልክ: 1300 135 500

Caxton Legal Centre Inc.
© Copyright Caxton Legal Centre Inc.
1 Manning Street
South Brisbane Qld 4101

ስልክ: (07) 3214 6333
ፋክስ: (07) 3846 7483
ኢንተርኔት: www.caxton.org.au

ይህ መረጃ በየካቲት/February 2019 ዓ.ም ላይ ወቅታዊ ነው።



## የክህደት ቃል

ይህ የመረጃ ዝርዝር ወረቀት ለአጠቃላይ መረጃ ብቻ ተብሎ የቀረበ እንጂ እንድ ህጋዊ የሆነ ምክርን የሚተካ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ይህ በሚጻፍበት ጊዜ ትክክለኛ እንዲሆን ማንኛውም ጥረት ቢካሄድም ህጉ የተወሳሰበ እና ያለማቋረጥ ተለዋዋጭ እንደሚሆን ነው።

አንድ ሰው በዚህ መረጃ ወይም ከዚህ ጽሁፍ ማስወገድ ተመርኩዞ በደረሰበት ማንኛውም ኪሳራ፤ በደል ወይም ጉዳት፤ የፋይናንሻል ወይም ሌላ ችግር የተቀባይነት ሀላፊነት የለም።